yx¤T×eÃ ØÁ‰§êE Ä¤äK‰s¤ÃêE ¶pBl¤K

ØÁ‰L nU¶T Uz¤È

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራስድስተኛ ዓመት q_R $ አዲስ አበባ ነሐሴ 03 qN 2ሺ.2 ዓ.ም	bx¤T×eÃ ØÁ‰§êE Ä¤äK‰s¤ÃêE ¶pBl¤K የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	16th Year No. 50 ADDIS ABABA 19th August, 2010

¥WÅ	CONTENTS
xêJ q_R 6)(/2ሺ.2 ›.M	**Proclamation No. 690/2010**
የማኅበራዊ ጤና መድህን አዋጅ ......ገጽ 5¹¼4)(4	Social Health Insurance Proclamation Page 5494

PROCLAMATION NO. 690/2010.

xêJ q_R 6)(/2ሺ.2

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR SOCIAL HEALTH INSURANCE

ስለማኅበራዊ ጤና መድኅን የወጣ አዋጅ

WHEREAS, expansion of health service coverage plays a significant role to an accelerated socio-economic development of the country;

የጤና አገልግሎት ሽፋን መስፋፋት ለአገሪቱ የተቀላጠፈ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ጉልህ ድርሻ ያለው መሆኑን በመገንዘብ፤

WHEREAS, cost sharing between beneficiaries and government in the health sector is critical to achieve universal health care coverage;

ሁሉን አቀፍ የሆነ የጤና ሽፋንን ለማረጋገጥ በመንግሥትና በተጠቃሚው ኅብረተሰብ መካከል ወጪን መጋራት ወሳኝ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, social health insurance is one of the sustainable health care financing mechanisms which enhances equitable access to improved health services through cross-subsidization;

የማኅበራዊ ጤና መድህን በአባላት መካከል መደጋገፍን በመፍጠር ፍትሃዊና የተሻለ የጤና አገልግሎትን ለማኅልበት የሚረዳ ቀጣይነት ያለው የጤና ፋይናንስ ማሰባሰቢያ ስልት በመሆኑ፤

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ $5 ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

PART ONE GENERAL

ክፍል አንድ ጠቅላላ

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Social Health Insurance Proclamation No.690 /2010."

1. አጭር ርእስ

ይህ አዋጅ "የማኅበራዊ ጤና መድህን አዋጅ ቁጥር 6)(/2ሺ.2" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1/ "አሠሪ" ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም ቢያንስ 0 ሠራተኞችን ቀጥሮ የሚያሰራ ማንኛውም ሰው ነው፤

2/ "ሠራተኛ" ማለት ሦስት ወርና ከዚያ በላይ አገልግሎት ያለው ማንኛውም ሠራተኛ ሲሆን የመንግሥት ባለሥልጣንን፣ የሥራ መሪን፣ ዳኛን፣ ዐቃቤ ሕግን፣ የፖሊስ አባልን፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልን፣ ደመወዝ ተከፋይ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባልንና ደመወዝ ተከፋይ የሠራተኛ ማኅበር ተመራጭን ይጨምራል፣ ሆኖም የመከላከያ ሠራዊት አባልን አይጨምርም፤

3/ "የጡረታ ባለመብት" ማለት ማንኛውም ከማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ወርሃዊ አበል የሚከፈለው ሰው ሲሆን የጡረታ ባለመብቱን ተተኪዎችም ይጨምራል፤

4/ "የጤና አገልግሎት ተቋም" ማለት ማንኛውም ለተጠቃሚዎች አገልግሎት ለመስጠት ከኤጀንሲው ጋር ውል የገባ የጤና ተቋም ነው፤

5/ "አባል" ማለት ለጤና መድህኑ የተመዘገበና ለመድህኑ መዋጮ የሚያደርግ ሠራተኛ ወይም የጡረታ ባለመብት ነው፤

6/ "ደመወዝ" ማለት ሠራተኛ ለአሠሪው በመደበኛ የሥራ ሰዓት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚከፈለው ወርሃዊ ክፍያ ነው፤

7/ "ተጠቃሚ" ማለት በማህበራዊ ጤና መድህኑ አማካኝነት የህክምና አገልግሎት የማግኘት መብት ያለው ሰው ነው፤

8/ "ልጅ" ማለት ዕድሜው ከ08 ዓመት በታች የሆነ የአባል የስጋ፣ የእንጀራ ወይም የጉዲፈቻ ልጅ ሲሆን አባሉ በህግ መሠረት የአሳዳጊነት ኃላፊነት የተጣለበትን ማንኛውንም ልጅ ይጨምራል፤

9/ "የትዳር አጋር" ማለት ከአባል ጋር በጋብቻ የተሳሰረ ሰው ነው፤

0/ "ቤተሰብ" ማለት የአባልን የትዳር አጋርና ልጆችን የሚያጠቃልል ሲሆን ዕድሜያቸው ከ08 ዓመት ያላነሰ ቢሆንም ራሳቸውን ለማስተዳደር የማይችሉ የአእምሮ በሽተኛ ወይም የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ልጆችን ይጨምራል፤

1/ "employer" means a public office, a public enterprise or any person that employs at least ten employees;

2/ "employee" means any employee having a three month and above period of service and includes public officials, management staff, judges, prosecutors, members of the police, members of the House of Peoples' Representatives, salaried members of the House of the Federation and salaried labor union officials, and may not include members of the Defense Forces;

3/ "pensioner" means any person receiving monthly pension payments from the Social Security Agency and includes survivors of a pensioner;

4/ "health facility" means any health facility that have concluded an agreement with the Agency to provide services for beneficiaries;

5/ "member" means a person registered for the social health insurance scheme and paying contribution to the scheme;

6/ "salary" means the monthly remuneration paid to an employee for the service he renders during regular working hours;

7/ "beneficiary" means a person entitled to receive the benefit packages under the social health insurance scheme;

8/ "child" means the natural, adopted or stepchild of a member who has not attained the age of 18 years and includes any child who is under the guardianship of the member in accordance with the law;

9/ "spouse" means a person married to a member;

10/ "family" comprises the spouse and children of a member and includes mentally or physically impaired children of the member who have attained the age of 18 years but cannot sustain themselves;

01/ "የጤና አገልግሎት ፓኬጅ" ማለት በማኅበራዊ ጤና መድህን ሥርዓቱ የሚሸፈኑ የጤና አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፤

02/ "ኤጀንሲ" ማለት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚቋቋም ኤጀንሲ ነው፤

03/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

04/ ማናቸውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

ክፍል ሁለት
የማኅበራዊ ጤና መድህን ሥርዓት

3. መቋቋም

የማኅበራዊ ጤና መድህን ሥርዓት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

4. ዓላማ

የማኅበራዊ ጤና መድህን ሥርዓት ዓላማ ተጠቃሚው በጤና ተቋማት አገልግሎት በሚሻበት ወቅት አብዛኛውን ከኪስ የሚከፈል ወጪ በመቀነስ ጥራት ያለውና ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ሽፋን ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲያገኝ ማድረግ ይሆናል።

5. አባልነት

1/ ሠራተኞችና የጡረታ ባለመብቶች የማኅበራዊ የጤና መድህን ሥርዓት አባላት ይሆናሉ።

2/ ማንኛውም አሠሪ ሠራተኞቹን ለማኅበራዊ የጤና መድህን በኤጀንሲው ዘንድ ማስመዝገብ ይኖርበታል።

3/ የማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ሁሉንም የጡረታ ባለመብቶች ለማኅበራዊ የጤና መድህን በኤጀንሲው ዘንድ ማስመዝገብ ይኖርበታል።

4/ ኤጀንሲው የአባላትን አመዘጋገብ በተመለከተ መመሪያዎችን ያወጣል።

11/ "health service package" means health services covered by the social health insurance scheme;

12/ "Agency" means an agency established by regulation to be issued by the Council of Ministers for the implementation of this Proclamation;

13/ "person" means any natural or juridical person;

14/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

PART TWO
SOCIAL HEALTH INSURANCE SCHEME

3. Establishment

A social health insurance scheme is hereby established.

4. Objective

The objective of the social health insurance scheme shall be to provide quality and sustainable universal health care coverage to the beneficiary through pooling of risks and reducing financial barriers at the point of service delivery.

5. Membership

1/ Employees and pensioners shall be members of the social health insurance scheme.

2/ Every employer shall get registered all its employees with the Agency for the social health insurance scheme.

3/ The Social Security Agency shall get registered all pensioners with the Agency.

4/ The Agency shall provide guidelines on registration of members.

6. የፋይናንስ ምንጮች

የማኅበራዊ ጤና መድህን ሥርዓት የሚከተሉት የፋይናንስ ምንጮች ይኖሩታል፡-

1/ የአባላት መዋጮ፤

2/ የአሠሪዎች መዋጮ፤

3/ ከኢንቨስትመንት የሚገኝ ገቢ፤ እና

4/ ሌሎች ተያያZነት ያላቸው ምንጮች።

7. ተጠቃሚዎች

1/ የማኅበራዊ ጤና መድህን ሥርዓት ተጠቃሚዎች አባላትና ቤተሰቦቻቸው ይሆናሉ።

2/ ማንኛውም አባል ስለቤተሰቡ ትክክለኛ መረጃ የመስጠትና አገልግሎቱን በአግባቡ የመጠቀም ግዴታ አለበት።

8. የጤና አገልግሎት ፓኬጅ

1/ ለተጠቃሚዎች የሚሰጠው የጤና አገልግሎት ፓኬጅ መሠረታዊ የጤና አገልግሎቶችንና ወሳኝ የሆኑ ሌሎች የፈውስ ህክምናዎችን የሚያካትት ይሆናል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው የጤና አገልግሎት ፓኬጅ ዝርዝር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሠረት የሚሰበሰበውን መዋጮ ግምት ውስጥ በማስገባት በደንብ ይወሰናል።

9. መዋጮ

1/ አባላትና አሠሪዎች ለማኅበራዊ የጤና መድህን ሥርዓቱ ወርሃዊ መዋጮ ያደርጋሉ። መንግሥትም ለጡረታ ባለመብቶች ተጨማሪ መዋጮ ያደርጋል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚከፈለው መዋጮ መጠንና አከፋፈሉ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፤ ሆኖም ሠራተኛና አሠሪ በሠራተኛው ደመወዝ ላይ የተመሠረተ እኩል የሆነ መቶኛ ይከፍላሉ።

6. Sources of Finance

The social health insurance scheme shall have the following sources of finance:

1/ members' contributions;

2/ employers' contributions;

3/ investment income; and

4/ other related sources.

7. Beneficiaries

1/ Beneficiaries of the social health insurance scheme shall be members and their families.

2/ Any member shall have the obligation to provide accurate information about his family composition and use the service properly.

8. Health Service Package

1/ The health service package to be provided to beneficiaries shall include essential health services and other critical curative services.

2/ The particulars of the health service package referred to in sub-article (1) of this Article shall be determined by regulation taking into consideration the contributions to be collected pursuant to Article 9 of this Proclamation.

9. Contributions

1/ Members and employers shall contribute to the social health insurance. The Government shall also make additional contributions for pensioners.

2/ The amount and payment modality of contributions to be made pursuant to sub-article (1) of this Article shall be determined by regulation to be issued for the implementation of this Proclamation; provided, however, that an employee and employer shall make equal percentage contributions based on the salary of the employee.

3/ ማንኛውም አሠሪ በየወሩ ሠራተኛው መክፈል የሚገባውን መዋጮ ከደመወዙ ቀንሶና ከራሱ የሚጠበቅበትን መዋጮ ጨምሮ በወቅቱ ለኤጀንሲው ማስተላለፍ አለበት።

4/ የማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የጡረታ ባለ መብቶችን ወርሃዊ መዋጮና መንግሥት ለጡረታ ባለመብቶች የሚያደርገውን ተጨማሪ መዋጮ ለኤጀንሲው ያስተላ ልፋል።

5/ ወርሃዊ የጡረታ አበሉ ሳይቋረጥ እንደገና ተቀጥሮ በመሥራት ላይ ያለ የጡረታ ባለመብት ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም እንደ ሠራተኛ ይቆጠራል።

6/ ማንኛውም አሠሪ ኤጀንሲው በሚፈልገው መሠረት ስለእያንዳንዱ ሠራተኛ ደመወ ዝና ተያያZነት ያላቸው መረጃዎች የመስ ጠት ግዴታ አለበት።

ክፍል ሦስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

0. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

01. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

1/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አወጅ ውስጥ በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነ ገገው ቢኖርም፡-

ሀ/ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 3)&7/09)(6ን መሠረት በማድረግ በኅብ ረት ስምምነት የሚሰጡ ተጨማሪ የጤና አገልግሎት ጥቅሞችን፣ እና

ለ/ በፖሊስ የጤና ተቋማት ለፖሊስ አባ ላት የሚሰጡ ተጨማሪ የጤና አገልግ ሎት ጥቅሞችን፣

ይህ አዋጅ አያስቀርም።

3/ Any employer shall withhold the contributions of employees from their monthly salaries and timely transfer the same to the Agency together with its own matching contributions.

4/ The Social Security Agency shall transfer to the Agency the monthly contributions of pensioners together with the matching contributions of the government.

5/ Any pensioner who is re-employed without foregoing his monthly pension allowance shall be considered as an employee for the purpose of this Article.

6/ Any employer shall furnish the Agency with particulars regarding each employee's salary and other related information as may be required by the Agency.

PART THREE
MISCELLANEOUS PROVISIONS

10. Power to Issue Regulation

The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

11. Inapplicable Laws

1/ No law, regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable in respect of matters provided for by this Proclamation.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, this Proclamation shall not affect:

a) additional medical benefits granted under collective agreements concluded in accordance with the Labour Proclamation No. 377/2003; and

b) additional medical benefits granted by police health institutions to members of the police.

02. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ከአንድ ዓመት በኋላ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ 03 ቀን 2ሺ2 ዓ.ም

GR¥ wLdg|×Rg|S

yx|T×eÃ ØÁ‰§ê ÄÌäK‰s|Ãê ¶pBl|K PÊz|ÄNT

12. Effective Date

This Proclamation shall come into force a year after its publication in the Federal Negarit Gazeta..

Done at Addis Ababa, this 19th day of August, 2010

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA